# <u>መሰረተ ኃሳብ (1)</u>

## <u>የሲቪክ ማህበራት ይዘትና ሚና</u>

ግርማ እሸቴ

በአሁኑ ጊዜ የሲቪክ ማህበራት አስፈላጊነትን በተመለከት ብዙ ቢነገርም የእነዚህ ማህበራት ይዘታቸውና ሚናቸው ምን እንደሆነ ግን ያለው ግንዛቤ አነስተኛ ወይም የተዛባ በመሆኑ ማህበራ ቱ እንቅፋት ሲያጋጥማቸው እናያለን፡፡ በየካቲት አብዮት ጊዜ የማህበራት ሚናና ተልዕኮ ከሞላ ጎደል የታወቀ ነበር ማለት እንደምንችልም ሲታወስ ከዚያም ጊዜ ጀምሮ በዚህ መስክ ብዙ ተመክሮ ተገብይቷል፡፡

ይህም በቅድሚያ የንቃትና እውቀትን አስፈላጊነት ተገቢውን ቦታ እንድንሰጠው የሚጠይቀን ይሆናል፡፡ ቀደም በቲዎሪና ርዕዩተ ዓለም ግንዛቤ ላይ ሙሉ ትኩረት ስለነበርና የፖለቲካ ግንዛቤ ም ቢሆን ከፍ ያለ በመሆኑ በአሰተሳሰብ ደረጃ ብዙ መደናገር አልነበረም፡፡ ዛሬ ግን ሁኔታዎች ተለውጠው በተለይም ንቃትና እውቀትን በተመለከተ አሉታዊ ግምት ሰፍኖ ስለ ድርጅት ሆነ ሲቪክ ማህበራት ሀ ሁ ን የማናውቅ ሆነን አያያዝም አካሄድም እየተወላገደ ጉዞ ሳንጀምር መውደቅ በርክቶብናል፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ ሲቪክ ማህበራት ስንል ምን ማለታችን መሆኑን መመለስ አለብን ማለት ነው፡፡ ሲሺክ ህብረተሰብ ማለትም ሰራተኛው በአጠቃላይ፤ሴት ወንዱ፤ አርሶ አደሩ ወዘተ ነው፡፡ በፖለቲካ ድርጅት ሳይሆን በማህበራት ሲደራጅ (የሰራተኞች ማህብር፤ የሴቶች ማህበር፤ የአስተማሪዎች ማህበር፤ልዩ ልዩ መረዳጃ ማህበራት ወዘተ) በሲቪሉ ማህበራት ደረጃ ተሰባሰበ ይባላል፡፡ ሲቪል ህብረተ ሰቡ (ሲቪል ሶሳየቲ) በማህበራት ተደራጅቶ በሀገሪቷ መንቀሳቀስ መቻሉ የሕዝብን ሰፋ ያለ ተሳትፎ (ማለትም በፖለቲካ ድርጅቶች ካለው በተለየ ) ያረጋግጣል፡፡ህብረተሰቡ በሀገሩ አጠቃላይ የፖለቲካና ሌላም መድረክ ብቅ ብሎ ወሳኝ ሚና ካልተጫወተ የሀገር ፖለቲካ በጥቂቶች፤ በምርጦች፤ በፖለቲከኞች ብቻ የሚወሰን ይሆናል፡፡ መድረኩ ይጠባል፡፡

የሲቪክ ማህበራት ይዘት ና አደረጃጀት የህብረተ ሰቡ ክፍሎችን መለያ ይመለከታል፡፡ ሠራተኞ ች በሰራተኛነታቸው፤ ሴቶች በሴትነታቸው፤ ተማሪና አስተማሪው በዚሁ ሙያቸው መሰረት የሚ ደራጁ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በፖለቲካ አቅዋማቸው መሰረት ተለይተው የሚቋቋሙ አይደሉም፡፡ የልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት የተወሰነ ማህበር (የ ሴቶች፤ ሰራተኞች ወዘተ ) አባል መሆን ይችላሉ፡፡ ይህ ማለት ግን ማህበሩ ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት ታዛዥና ተገዢ ነው ማለት አይደለም፡፡የፖለቲካ ድርጅቶች የፉክክር ዋና መድረክ የሲቪክ ማህበራት ውስጥ ሊሆን አይገባ ውም፡፡ በሌላ በኩል የተወሰነ ማህበር አባላት ድጋፋቸውን ለሆነ ድርጅት መስጠት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የእንግሊዙ ትሬድ ዩኒየን ኮንግሬስ የሰራተኛ ማህበር የሌበር ፓርቲ ደጋፊ ነው፤ የአሜሪ ካው ኤ ኤፍ ኤል ሲ አይ ኦ ለዴሞክራቲክ ፓርቲ ድጋፉን ይሰጣል፤ የጣሊያንና የፈረንሳይ

ትላልቆቹ የሰራተኛ ማህበራት (ሲጂአይኤል ና ሲጂቲ) ለኮሙኒስት ፓርቲዎች ሙሉ ድጋፍ
ይሰጣሉ፡፡ በየካቲት 66 ተማሪዎች፣ አስተማሪዎችና ሰራተኞች ከነማህበሮቻቸው ለኢሕአፓ
ድጋፍ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ሰራተኛው በመደቡ በፖለቲካው መስክም የማይናቅ ሚና ያለው
ነውና ኤኮኖሚያዊና አልፎም ፖለቲካው ትግል ማካሄዱ የተለመደና የሚጠበቅ ነው፡፡ የማህበራ
ቱ ድጋፍና ዝንባሌ እንዳለ ሆኖ ድርጅታዊ ነፃነታቸው ግን የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡ የማህበራ
ትን ነፃነት የሚፃረሩ አምባገነን አገዛዞች በምስላቸው ማለትም በራሳቸው እዝና ቁጥጥር ስር
የሚሆኑ  ማህበራትን ይመሰርታሉ፡፡

የሲቪክ ማህበራት ምንም የፖለቲካ ሚና ሊኖራቸው አይችልም የሚለው አስተሳሰብ የተሳሳተ
ቢሆንም ዋናው ሚናቸው የአባላትን ማህበረሰባዊና አልፎም ኤኮኖሚያዊ ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡
ለምሳሌ ሴቶች በማህበር ሲደራጁ በቅድሚያ የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ መታገል በሚል
መርህ ግብር ዙሪያ የሚሰባሰቡ በመሆናቸው በሴትነታቸው ብዙዎች አባል ይሆናሉ፡፡ አመጣጣቸ
ውና ዝንባሌያቸው ከልዩ ልዩ ፖለቲካ ድርጅቶች የተያያዘ ወይም ያልተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡
ዋናው የሚያስተሳስራቸው ግብ ግን የሴቶችን እኩልነት ማረጋገጥ፣ ለመብት መታገል፣ ሴቶችን
መርዳት ወዘተ ነውና ባላቸው የተለያየ የፖለቲካ አቅዋም መሰረት ሊጋጩና ሊለያዩ በር መክፈ
ት የለባቸውም ማለት ነው፡፡ ያሉት አምባገነን አገዛዞች የራሳቸው የሴቶች፣ የሰራተኞች፣ የተማሪ
ና የአስተማሪ ተለጣፊ ማህበራት በሚያቋቁሙበት ጊዜም እነዚህን ታግሎ ነፃ ማህበራትን መመሰ
ረትና ማሳደግ ግዴታ ይሆናል፡፡ የማህበራቱ መሰባሰቢያ መለስተኛ መርህ ግብር በተወሰነ ርዕዩተ
ዓለም ላይ የተመሰረተ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ዓይነት አደረጃጀት የሚተወው ለፖለቲካ ድርጅ
ቶች ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ያለውን ሁኔታ ስንመረምር ደግሞ ራሳቸውን የፖለቲካ ድርጅት ብለው
ግልፅ መርህ ግብርም ሆነ አሰባሳቢ አቅዋም የሌላቸው ብዙዎች ናቸው፡፡ ነፃ ገበያ፣ ሊበራል ካፒ
ታሊዝም ፣ሶሻል ዴሞክራሲ የሚሉ ቅፅሎችን ለጥፈው ዛሬ በሀገራችን መሬት ህጋዊም ሆነው
የተሰለፉት ድርጅቶች በተጨባጭ አቅዋም ደረጃ መርህ ያሉትን ሁሉም ሲያስተጋቡ አይታዩም፡፡
ቀኝ ክንፍ የመሆን መብታቸውን ሲያስረግጡ ግራ ክንፍ የመሆንን መብት መርገጥ ይመኛሉ፣
ይፈልጋሉ፡፡ ዴሞክራሲያዊ ነን እያሉ በፆታ ፣በሀይማኖትና ብሄረሰበ መሰረት ልዩነት ያደርጋሉ፡፡
ማህበራት በበኩላቸው ከዚህ ዓይነቱና ከፖለቲካዊ ግብግብ የራቁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሲቪክ
ማህበራትና ድርጅቶች  መሀል ሊኖር የሚገባው ትስስር ወይም ዝምድና በፈቃደኛነትና በአርአያ
ነት ላይ የተመሰረተ  መሆን ይገባዋል እንጂ በተፅዕኖና ሰርጎ ገቦችን አሰማርቶና ሻጥር አካሂዶ
የማህበሩን ነፃነት በማፍረስ/በመቀማት አይደለም፡፡ ድርጅቶችም ፉክክራቸውን በሲቪክ ማህበራ
ት ውስጥ ማካሄድ አይገባቸውም፡፡ የየራሳቸው የሴቶች፣ የወጣቶች ወዘተ ማህበር ማቋቋም
መብታቸው ሲሆን ህብረተሰቡ ግን በሞያና በፆታ በስፋትና ሁሉን አቀፍ መርህ ግብርን አስቀድ
ሞ የመሰረታቸውን ማህበራት ማገዝ እንጂ በግዴታ በቁጥጥር ስር ማስገባት የድርጅቶች ግብ
ሊሆን አይችልም/አይገባም፡፡

በአሁኑ ወቅት ወያኔ ነፃ ማህበራትን አግዶና አፍርሶ በራሱ ሙሉ ቁጥጥር ስር ያሉ ተለጣፊ ማህበ ራትን መስርቷል። ይህን በሁለት መልኩ መታገል መሞከር አለብን ማለት ነው። 1ኛ/ የወያኔን ቁጥጥር ከነዚህ ማህበራት ጫንቃ ላይ ለማስወገድ በስልት መታገል፤ 2ኛ/ ሌሎች ነፃ ማህበራትን በህቡዕም ቢሆን መመስረት። የነፃ መደራጀት መብት እንዲከበር ትግልን ማጧጧፍና በተለይም ሸንካላ ዴሞክራሲን (ለጥቂቶች ውሱን መብትን እየለገስ ብዙሃኑን የሚያገልና መብት የሚያፍን) ማውገዝ አስፈላጊ ነው። ለእኛ ከተመቸ ለሌላው ምን ገዶን አቅዋም ሀገርን ይጎዳል። የሲቪክ ማህበራት መመስረትና መጠናከር ሰፊው ሕዝብ በሀገሪቷ ጉዳይ የነቃ ተሳትፎን ያረግ ዘንድ የሚ ያግዝ፤ የሚረዳና የሚያረጋግጥ ነው። ለዚህም ነው ህብረተሰቡ በየፈርጁ እንዲደራጅና ማህበራቱ ም እንዲጠናከሩ መጣር ያለብን። አንዳንዶች ሲቪክ ማህበራት የፖለቲካ ድርጅቶችን ተክተው ሲታገሉ ይታያቸዋል-- ይህ ግን ከባድ ስህተት ነው። ድርጅት አያስፈልግም በሚል የቀቢፀ ተስፋ ውልድ በሆነ ፈሊጥ ማህበራትን በፖለቲካ ድርጅት ቦታ ሊያሰቀምጡ የሚጥሩ ትግላችንን ይጎዳሉ። የሲቪክ ማህበራት ጉልህ ሚና ከተረጋገጠ የፖለቲካ ድርጅቶችን ትግልን ያደምቃል፤ የፖለቲካ ድርጅቶችን ለማጠናከር በማህበራት የተደራሸ ሲቪል ህበረተሰብ መኖሩ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው። ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ከተጠናከሩ ደግሞ የሲቪሉ ህበረተሰብ ተሳትፎና ማህበራት ሚናቸውን ይወጣሉ። ለማንኛውም ሕዝባዊ ትግል ሕዝብን ማቀፍ አለበትና ህብረተሰቡ በድርጅቶችም ሆነ በማህበራት እየተሰባሰበበ ፈርጀ ብዙ ሁለገብ ትግልን ማካሄድ መቻል አለበት። የድል ዋስትና የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ ነው።